# የምዕራብ ካናዳ ኢሕአፓ ዴሞክራሲያዊ
# ስለ ኢትዮጵያ 2015 ምርጫ የተሰጠ መግለጫ
## ግንቦት 30 2015

## “ ለስሟ መጠሪያ ቁና ሰፋች “
## ድንቄም ዲሞክራሲያዊ ምርጫ

የምዕራብ ካናዳ ኢህአፓዴ የአገራችንን ህዝብ መሳለቂያ ያደረገው የምርጫ ትእይንት በህዝባችን ላይ ያወረደው እመቃ እና ሰቆቃ መባባሱን እንጂ ዲሞክራሲያዊ ሂደት በኅጠኝነት መንፈስ እራሱን ባደራጀ ሀይል ይመጣል የሚል ቅዠት ውስጥ ዋዥቆም አያውቅም ። በዚህ ሂደት ሀየወታቸውን አካላቸውን እና የኑሮ ህልውናቸውን በምርጫ ሰበብ አጥተው ለሚንገላቱ ወገኖች ግን ከጎናቸው አብረን እንቆማለን ። በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ እራሱን የሾመው የጥቂት ጎሰኞች የዘረፋና የጭፍጨፋ ቡድን በየጊዜው እየተነሱበት የመጡትን ህዝባዊ እመቢተኝነት ለማፈንና ለማጥፋት የተለያዩ የጭቆና ስልቶችን ሲጠቀም መቆየቱ ለማንኛውም ወገን የተሰወረ አይደለም በተለይም የስርዓቱ ሰለባ የሆኑትና 24 አመታት ሙሉ በስደትና በእስር ስቃዩን የቀመሱት አገራችንና ዜጎቿ ህያው ምስክሮች ናቸው። የኢትዮጵያ ህዘብ ላለፉት በርካታ ዓመታት የፖለቲካ፤ የኢኮኖሚና የማህበራዊ እኩልነት መብቱን ለማስከበር የከፈለው መስዋዕትነት ከንቱ እንዲሆን ያደረጉት ሀይሎች ስልጣን ለመቆናጠጥ የሚያስችላቸውን ማደናገሪያ አጀንዳዎች በማራገብ እና ሁለንተናዊ ለውጥ የሚጠይቁ ሀይሎችን በመግደል እና ሰፊው ሕዝብም ነጻ የሆነ መገናኛ ብዙሀን እንዳይኖረው ሌት ተቀን በመስራታቸው ነው ።

አገራችን ኢትዮጵያ ዲሞክራሲን የምትሻው በሽርፍርፉ ለይስሙላ ሳይሆን እንደምግብ እንደውሃ እንደ አየር ለህልውናዋ አስፈላጊ ከመሆኑም አልፎ ያሏትን ታዳጊ ወጣቶች ፍላጎት ሊያስተናግድ የሚችል፤
የሀያ አንደኛው ክፍለዘምን የፖለቲካ አስተዳደር መንገድ በመሆኑ ነው የዚህ ዓይነት አስተሳሰብ ሊመጣ የሚችለው ደግሞ በጡንቻ ልዩነትን እና ቅዋሜን ለመፍታት በሚያምን የአስራስድስተኛው ክፍለዘመን የኋልዮሽ ዓመለካከት አይደለም ። የቅርብ ጊዜያት የትግል ትውስታችን እንደሚያስረዳን ወታደራዊው መንግስት የኢትዮጵያን ሕዝብ ትግል በአየር ላይ የጠለፈውና የቀለበሰው መሬት ለአራሹ የሚባለውን ሕዝባዊ መፈክር ፊት በማስቀደም ያውም አውገርግሮ ሊመልሰው በሞከረው ጉዳይ እንደነበረ ስናስታውስ የወያኔውም ቡድን ከሁሉም የዲሞክራሲያዊ ጥያቄዎች አንዷን አጀንዳ ከሌሎች ዲሞክራሲያዊ ጥያቄዎች ተነጥሎ ሊመለስ የማይችለውን የብሔር ጥያቄ በማራገብ ስልጣኔን መርቁልኝ ዲሞክራሲያዊ መንግስት ነኝ ሲል ይሄው ሩብ ምዕተ ዓመታትን አባክኗል፤ ደርግንም ወያኔን አንድ የሚያደርጋቸው ሁለቱም መንግስት ገልብጠዋል ሁለቱም ምርጫ አድረገዋል ሁለቱም ነጻነት የላቸውም ለህዘቡም ነጻነትን ነፍገዋል። የደርግ ምርጫ ግለጽ ነው አንድ ፓርቲ ሌላም አጃቢ ያላሳተፈ ሲሆን

የወያኔ ግን ብዙ ድካም እና አጫፋሪ ድራማ የተደገፈ ነበር። አሳዛኙ ግን የምርጫው ድራማ ጸሀፊ ምን ያህል የጀማሪ ደራሲ እንኳን ብቃት እንደሌለው የብእር አጣጣሉን ጫፍ ያየ መጨረሻው መደምደሚያ
ምን ሊሆን እንደሚችል ማወቅ የሚችልበት መሆኑ ነበር፤ ኢትዮጵያን ወደ ምርጫ ዲሞክራሲ ለማምጣት እንቅፋት ሲተበትብ የኖረው ኻሰኛ ቡድን የ2015 የምርጫ ዝግጅትን የጀመረው በመሰረቱ ከአመሰራረቱ መሆኑ ቢታወቅም ቀረብ ያሉትን ሸፍጦች ብናይ በዲሞክራሲ ጉልበታ ውስጥ ሚና የሚኖራቸውን እሴቶች እንደ ነጻ የፍርድ ስርዐት እና ነጻ ምረጫ አስፈጻሚ፤ ነጻ ሚዲያዎች እና ጋዜጦችን መዝጋት፤ ጋዜጠኞችን ማዋከብ ማሰር ማደህየት እና ማሳደድ፤ የፖለቲካ እይታቸው ዲሞክራሲያዊ እና አገራዊ የሆኑ የፖለቲካ ፓርቲዎች እና ግለሰቦችን ማሰር መወንጀል እና ሰርተው እንኳን እንዳይኖሩ በራሳቸውና በቤተሰቦቻቸው ህይወት ላይ መፍረድ፤ የመንግሰት ሰራተኛው በሙያውና በአገር ዜግነቱ ሰርቶ የመኖር መብቱን ነጥቆ የድርጅት ታማኝነት ግዴታዎችን መመዘኛ አድርገው የሰራተኛውን ነጻነት መንጠቅ፤ ነጻ የሙያ ማህበራት እንዳይኖሩ ታማኝ ካድሬዎች በብዙሀኑ ሰራተኛ ላይ በማስቀመጥ የማፈኛ ስራቻውን ማጠናከር፤ አገሪቱ በድህነት ቅነሳ መርሀ ግብር የምታገኛቸውን የልገሳ ገንዘብና አለማቀፋዊ ብድሮች በመጠቀም የሚሰሩ መሰረታዊ እና ማህበራዊ አገልግሎት መስጫ ተቋማት ግንባታዎች መንግስት ተብየው በፈጠረው የኢኮኖሚ እድገት የተገኙ አስመስሎ በሚቆጣጠራው የመንግሰትና ባደራጃቸው ቀለብ ተሰፋሪ ሚዲያዎች ማደናቆር፤ የኢትዮጵያ ህዘብ የሚኖርበት የድህነት ክፍትተ የፈጠረው መጠነ ሰፊ የኑሮ ችግር ህዝቡ ለዳቦ ሲል አንድ ላምስት የስለላ እና የህዝብ ማፈኛ መዋቅሮችን በመጠቀም፤ ዓለም አቀፍ ደጋፊ ለማግኘት በምርጫ የሚተዳደር መንግሰት ለመምሰል ሲያደርጋቸው ከነበሩት የድራማው ገጸ ባህሪያት ጥቂቶቹ እነደነበሩ እየታወቁ ሌሎች አገራት እንደሚያደርጉት ምርጫዎች፤
የኢትዮጵያ ገዠዎችም አይናቸውን በጨው አጥበው ብቅ ማለታቸው የሚያሳዝንም የሚያሳፍረም ከመሆን በላይ ጥሩ ተረት ተረት የላም በረት የሚባለውን የሕጻናት ቧልት እንኳን ያልመጠነ የምርጫ ሂደት ነበረ። ሁሌም የምናዝነው አካባቢያችን ካሉት ሀገራት እንኳን በምን የእድገት ደረጃ የምንገኝ መሆናችንን ህዝቡ እንዳያገናዝብ ሀያ አራት ሰአታት የማደናገሪያ ፕሮፓጋንዳ በ ኢቲቪና በሌሎች መዋቅሮች መዠጎድጎዱ ነው፤ ዩጋንዳ፤ ኬንያ፤ ታንዛኒያ መንገድ የሌላቸው ውሃ ጠምቷቸው የሚሞቱ አስመስሎ እድገት እንኳን ቢኖር ከማንንም የማያስበልጥ እንዲያውም የሚያሰቆጭ ከመሆን ለማይዘል እውነታ መመጻደቅ ትዝብት ነው።
ኢትዮጵያ ሀገራችን ባለንበት ክፍለዘመን መስፈርት የምትመዘን በመሆኗ የተፈለገው ማጭበርበር ተደርጎ በምርጫ የመጣሁ መንግስት ነኝ ቢባል እራስን ትዝብት ውስጥ ከመጣል የሚያስገኘው አንዳች ፋይዳ የለም። ከሁሉም በላይ የችግር ገፈቱን እየቀመሰ ያለው ሕዝባችን ድምጹን እየታፈነ ለዘመናት ይገዛልናል ማለት የክረምቱን ቁር ለመቋቋም ቦምብን እና ፍልጥ አደባልቆ እሳት እንደመሞቅ ያህል የዋህነት ነው እንላለን ።
የስልጣን ምንጭ ሕዝብ ነው!!!